# 1.ኖላዊ ትጉኅ

ኖላዊ ትጉኅ ዘኢትነውም /2/

ማኅበረነ /2/ ዕቀብ በሠላም /4/

የማታንቀላፋ ትጉህ እረኛችን /2/

ጠብቅልን በሰላም ማኅበራችንን /2/

# 2.አንቺ ነሽ ተስፋው

አንቺ ነሽ ተስፋው ለአዳም ኪዳነምሕረት /2/

በተሰደደ ጊዜ ከገነት /2/

# 3. ኦ ሚካኤል

ኦ ሚካኤል /2/ ሊቀ መላእክት

በኃጢአት እንዳንወድቅ እንዳንሞት

ፈጥነህ ተራዳን አጽናን በእምነት /2/

ለያዕቆብ ነገድ ሚካኤል

ለእስራኤል »

ጠባቂያቸው ነህ »

መልአከ ኃይል »

<u>ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል</u>

<u>የእኛ አባት</u> /2/

አዝ . . . . .

ነጸብራቃዊ ሚካኤል

ተክህኖ ልብስ »

ሐመልማለ ወርቅ »

ዓይኑ ዘርግብ »

<u>ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል</u>

<u>የእኛ አባት</u> /2/

አዝ . . . . .

በስእልህ ፊት ሚካኤል

እሰግዳለሁኝ »

ፈጥነህ አረጋጋን »

አለሁ በለን »

<u>ፍቅርን አድለን ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል</u>

<u>የእኛ አባት</u> /2/

አዝ . . . . .



## 4.ሚካኤል ሊቅ

ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቅ /2/

ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ /4/

ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ /2/



ትርጉም፦

አለቃ የሆነ ሚካኤል ልብሱ መብረቅ

ነው ዓይኖቹም የርግብ ዓይን ይመስላሉ

ሚካኤል የወርቅ ሐመልማል ነው